ህዳር 4 ቀን 2000 ዓ.ም

**ፕሬስ ሪልዝ**
**ህዳር 4 ቀን 2000 ዓ.ም**
**ማስታወቂያ ሚ/ር**

## የጥቂት ፀረ ሰላምና ፀረ ሕዝብ ኃይሎች ጩኸት የኢትዮጵያ ሕዝቦችን እውነተኛ ድምፅ ሊወክል አይችልም

ኤች አር 2003 ረቂቅ ሕግን አስመልክቶ በሃገር ውስጥና በውጪ ከፍተኛ የሕዝብ ተቃውሞ በተነሳባት በአሁኑ ወቅት ህዳር 3 ቀን 2000 ዓ.ም በአሜሪካ ኦክላሆማ ከተማ በቁጥር 75 የሚሆኑ ከፀረ ሕዝቦች ጋር የወገኑ ሰልፈኞች ረቂቅ ሕጉ እንዲፀድቅ መጠየቃቸው ሰልፉ በፀረ ሕዝብ ሃይሎች እንደተቀነባበረ በግልጽ አመላክቷል፡፡ ረቂቅ ሕጉ ከመዘጋጀቱ አንስቶ አሁን እስከአለበት ደረጃ ድረስ የኢትዮጵያን ውድቀት የሚሹ ፀረ ሰላም ሃይሎች እንደ ኦነግ፣ ኦብነግና ሻዕቢያን የመሳሰሉት ኃይሎች እጅ እንዳለበት ግልጽ ነው፡፡

ይህ ረቂቅ ህግ በአንዲት ሉዓላዊት አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ የሚገባ በመሆኑ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብን ያስቆጣ ነው፡፡ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ተከብሮ የሕዝቡ ተጠቃሚነት በተረጋገጠበት በአሁኑ ጊዜ ኤች አር 2003 እንዲፀድቅ መታገል የሕዝብ ወገናዊነትን ሳይሆን የለየለት ጠላትነትን በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ረቂቅ ህጉ የአገራችንን ነባራዊ ሁኔታና በኢትዮጵያና በአሜሪካ መካከል ያለውን ጠንካራ ግንኙነትና ትብብር ያላገናዘበ በመሆኑ በምንም ዓይነት መመዘኛ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም፡፡ እነዚህ ሰልፈኞች የፀረ ሕዝብና የፀረ ልማት ቡድኖችን ፍላጎት ለማሳካት ሰልፍ የወጡ ስለሆነ በምንም መልኩ የኢትዮጵያ ህዝቦችን ፍላጎትና ድምጽ ሊወክሉ አይችሉም፡፡ ከዚህ ይልቅ ባሁኑ ጊዜ ይህ ረቂቅ ህግ በአገር ውስጥና በውጭ በሚገኙ ኢትዮጵያውያን፣ ምሁራንና

የኢትዮጵያ ወዳጆች እየተወገዘና ተቀባይነት እንዳይኖረውም ከፍተኛ ግፊትና ተቃውሞ እያጋጠመው መሆኑን መረዳት ጠቃሚ ይሆናል፡፡

ይህም በመሆኑ ከኤች አር 2003 በስተጀርባ የተሰለፉ የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶች በህግ ረቂቁ ሽፋን በሚነዙት የጥላቻ ፕሮፓጋንዳና በሚያሰሙት ባዶ ጩኸት የሚያራምዱት የራሳቸው ድብቅ አጀንዳ ግቡን ሊመታ እንደማይችል ሊገነዘቡ ይገባል፡፡